መልእክት አራት

**መንፈስን በመተንፈስ፣ የሕይወትን ውኃ በመጠጣት**
**እና የእግዚአብሔርን እንጀራ በመብላት**
**የመለኮታዊውን ሥላሴ መለኮታዊ እደላ መለማመድ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዮሐ. 20፡22፤ 6፡33፣ 57፤ 1 ቆሮ. 10፡3-4፤ ራዕ. 2፡7፣ 17፤ 3፡20

**I. የተጠናቀቀው መንፈስ እንደ ቅዱሱ እስትንፋስ በትንሣኤ በወልድ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ተተንፍሷል—ዮሐ. 20፡22፡-**

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር በግ ለመሆን ክርስቶስ ሥጋ እንደሆነና በትንሣኤ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ እንደሆነ ይገልጣል፤ ከዚህም የተነሣ፣ በትንሣኤው እንደተጠናቀቀው መንፈስ ራሱን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ተንፍሷል—1፡29፤ 20፡22፡-

1. በ20፡22 መንፈስ ቅዱስ በ 7፡39 ሲጠበቅ የነበረው እና በ 14፡16-17፣ 26፤ 15፡26 እና 16፡7-8፣ 13 ቃል የተገባው መንፈስ ነው፤ ይህ የሚያመለክተው ጌታ መንፈስ ቅዱስን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ መተንፈሱ ሌላው አጽናኝ የመሰጠቱ ቃል ኪዳን ፍጻሜ እንደነበር ነው።
2. እርሱ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ የተተነፈሰው፣ በደቀ መዛሙርቱ ውስጥ መኖር የሚችለው እና እነርሱ በእርሱ እና ከእርሱ ጋር መኖር የሚችሉት፣ እርሱ በእነርሱ ውስጥ እነርሱም በእርሱ ውስጥ መኖር የሚችሉት እንደ መንፈስ ነው—20፡22፤ 14፡19-20፤ 15፡4-5።
3. መንፈስን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ በመተንፈስ፣ ጌታ ኢየሱስ እንደ ሕይወት እና እንደ ሁሉ ነገር ወደ እነርሱ ውስጥ ራሱን አስተላለፈ።
4. በ20፡22 ያለው መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ነው፣ ምክንያቱም ይህ መንፈስ የእርሱ እስትንፋስ ነውና፤ ስለዚህ፣ መንፈስ የወልድ እስትንፋስ ነው።

ለ. ጌታ ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ ነው፣ ይህም መንፈስ እስትንፋሳችን ነው—2 ቆሮ. 3፡6፣ 17፤ ዮሐ. 20፡22፡-

1. እግዚአብሔር የነበረው ቃል የእግዚአብሔር በግ ለመሆን ሥጋ ሆነ፣ በትንሣኤ እኛ ወደ ውስጥ እንተነፍሰው ዘንድ ቅዱሱ እስትንፋስ ሆነ—1፡29፤ 20፡22።
2. አሁን ክርስቶስ እንደ ቃል፣ በግ፣ ዛፍ እና እስትንፋስ አለን፡- ቃሉ ለመገለጥ ነው፣ በጉ ለቤዛነት ነው፣ ዛፉ ሕይወትን ለማስተላለፍ ነው፣ እስትንፋሱ ለኑሯችን ነው—1፡1፣ 29፤ 10፡10፤ 14፡19፤ 15፡1።

ሐ. የተጠናቀቀው መንፈስ እንደ እስትንፋስ የክርስትና ሕይወትን በመኖር ውስጥ ሁሉ ነገራችን ነው፤ ክርስቲያን መሆን የሚችለው እስትንፋሱ ብቻ ነው፣ ድል ነሺም መሆን የሚችለው እስትንፋሱ፣ መንፈሱ ብቻ ነው—ገላ. 3፡2-3፣ 14፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ራእ. 2፡7።

**II. የመለኮታዊውን ሥላሴ መለኮታዊ እደላ መለማመድ ከፈለግን፣ ሁላችንም አንዱን መንፈሳዊ መጠጥ፣ ክርስቶስን ሁሉን-እንዳካተተው ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ መጠጣት ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 10፡3-4፡-**

ሀ. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡4 ያለው መንፈሳዊ መጠጥ ከተመታው ዓለት የፈለቀውን ሕያው ውኃ ያመለክታል፤ ይህ ዓለት የተሰቀለውንና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል፣ ይህም ውኃ ሁሉን-እንዳካተተው መጠጣችን መንፈስን በምሳሌ ያሳያል—ዘጸ. 17፡6፤ ዮሐ. 7፡37-39፤ 1 ቆሮ. 12፡13።

ለ. መንፈሳዊው መጠጥ፣ ሕያዉ ውኃ በትንሣኤ ያለው የሕይወት ውኃ ነው፤ በትንሣኤ ያለውን የሕይወትን ውኃ ስንጠጣ በትንሣኤና ከትንሣኤ የሆኑ ሰዎች እንሆናለን—10፡4፤ ዮሐ. 14፡20፤ 2 ቆሮ. 1፡9።

ሐ. ክርስቶስን ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ በመጠጣታችን፣ እግዚአብሔር ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ይሠራል፣ ምክንያቱም በመጠጣት ጌታን ወደ ውስጥ እናስገባዋለን፣ እርሱም ሕይወታችንና ቅንብራችን ለመሆን ሕይወታዊ በሆነ መልኩ ከእኛ ጋር አንድ ይሆናል—1 ቆሮ. 10፡4፤ ቆላ. 3፡4፣ 10-11።

**III. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ክርስቶስን እንገልጠውና እንወክለው ዘንድ እርሱን እንደ የእግዚአብሔር እንጀራ እንድንበላውና በእርሱ እንድንቀናበር ነው—1 ጢሞ. 1፡4፤ ዮሐ. 6፡35፣ 41፣ 57፤ ዘፍ. 1፡26፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ በሕይወትና በባሕሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰውን ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ማድረግ ነው፤ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር እንጀራ በመብላት በሕይወትና በባሕርይ እግዚአብሔር እንሆናለን—ዮሐ. 6፡33።

ለ. በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ውጥን ራሱን ወደ ውስጣችን መሥራት እና ምግባችንን በመቀየርና ክርስቶስን እንደ ሰማያዊ ምግብ በመመገብ ቅንብራችንን መቀየር ነው—ዘጸ. 16፥14-15፤ ዮሐ. 6፥27፣ 32፣ 35።

ሐ. ዮሐንስ 6 ክርስቶስን እንደ እንጀራችን—ሰማያዊው እንጀራ፣ የሕይወት እንጀራ፣ ሕያው እንጀራ፣ እውነተኛ እንጀራ እና የእግዚአብሔር እንጀራ—ይገልጣል—ቁ. 32-33፣ 35፣ 41፣ 48፣ 50-51።

መ. ጌታ ኢየሱስ እንደ የእግዚአብሔር እንጀራ፣ የሕይወት እንጀራና ሕያው እንጀራ እርሱን እንድንበላው፣ እንድናብላላው እና እንድናዋሕደው ይፈልጋል—ቁ. 33፣ 35፣ 51፡-

1. የሕይወት እንጀራ በምግብ መልክ የሕይወት አቅርቦት ነው—ቁ. 35።
2. *የሕይወት እንጀራ* የእንጀራውን ባሕሪይ ያመለክታል፣ ያም ሕይወት ነው፤ *ሕያው እንጀራ* የእንጀራውን ሁኔታ ያመለክታል፣ ያም ሕያው ነው—ቁ. 35፣ 51።

ሠ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ክርስቶስ ውስጣዊ በሆነ መንገድ ወደ ውስጣችን የመምጣቱ ጉዳይ ነው፤ ለዚህ ክርስቶስን በመብላት እርሱን ማስገባት ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥17፤ ዮሐ. 6፥57፡-

1. መንፈሳዊ የሆነ መብላትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ዘገባ እግዚአብሔር ራሱን ሊያድለን የወጠነው በመብላት መንገድ እንደሆነ ይገልጣል—ቁ. 57፤ 1 ቆሮ. 10፥3፤ ራእ. 2፥7፤ 22፥14።
2. መብላት ከእኛ ውጪ የሆኑ ነገሮችን መገናኘትና ወደ ውስጣችን መቀበል ነው፣ ውጤቱም ቅንብራችን መሆናቸው ነው—ዘፍ. 2፥16-17።
3. ጌታ ኢየሱስን መብላት ዳግም በተወለደው አዲሱ ሰው በሕይወት መንገድ ከእኛ ጋር ይዋሐድ ዘንድ እርሱን ወደ ውስጣችን መቀበል ነው—ዮሐ. 6፥56-57።
4. ለመገለጡና ለመወከሉ የእግዚአብሔርን እደላ የምንለማመድበት መንገድ መብላት ነው—ዘፍ. 1፥26፤ 2፥9፤ ዮሐ. 6፥51፣ 53-57።
5. የበላነው፣ ያብላላነው እና ያዋሐድነው ምግብ በእርግጥ እኛን ይሆናል፤ ይህ የመዋሐድ ጉዳይ ነው—1 ቆሮ. 10፥17።
6. እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚፈልገው አንድነት ምግብ ስንበላ፣ ስናብላላ እና ስናዋሕድ በሚከናወነው ነገር በምሳሌ ቀርቧል—ዮሐ. 6፥57።
7. እኛ የምንበላውን ነን፤ ስለዚህ፣ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር እንጀራ ከበላነው፣ በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር እንሆናለን።

ረ. በራእይ 2 እና 3 ውስጥ ባለው የጌታ ቃል መሠረት፣ ድል ነሺዎቹ እንደ የምግብ አቅርቦታቸው ተገቢ ወደሆነው ጌታን መመገብ ተመልሰዋል፤ እንደ የሕይወት ዛፍ እና እንደተሰወረው መና ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በብልጥግናዎቹ እንደተሞላ ግብዣም ጭምር ይበሉታል—2፥7፣ 17፤ 3፥20።

*© 2022 Living Stream Ministry*